www.abyssinialaw.com



9ኛ አመት ቁጥር 51
9th Year No 51

ባህር ዳር _____ ቀን 1996 ዓ.ም
Bahir Dar _____, 2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር<br><br>Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312<br>P.o. Box |



| | |
|---|---|
| <u>ደንብ ቁጥር 21/1996 ዓ.ም</u><br>የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | <u>Regulation No. 21/2004</u><br>The Amhara National Regional State Commercial Registration and Business Licensing Proclamation Amendment Proclamation Implementation, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 21/1996 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅን ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 21/2004

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE IMPLEMENTATION OF COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING PROCLAMATION AMENDMENT PROCLAMATION IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



የኢፌዲሪ መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 ዓ.ም.ን አንዳንድ ድንጋጌዎች እንደገና በማሻሻሉና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ ድንጋጌዎችን በማካተት አዋጅ ቁጥር 376/1996 ዓ.ምን ህዳር 3 ቀን 1996 ዓ.ም ያወጣ በመሆኑ፤

WHEREAS, the Federal Democratic Republic Government of Ethiopia has amended some provisions of the commercial registration and licensing proclamation No. 67/1997 and issued proclamation No.376/2004 on November 10, 2004, incorporating other provisions necessary to encourage investment;

የማሻሻያ አዋጁ ፀድቆና ለክልላችን ደርሶ ወደ ተግባር የተገባው ዘግይቶ በመሆኑና ሁሉም የክልሉ ነጋዴዎችና አስፈፃሚ አካላት ሙሉ ግንዛቤ ካለመያዛቸው የተነሣ ብዛት ያለው ነጋዴ እስካሁን ድረስ ፈቃዱን በአዲሱ አዋጅ መሠረት ያላሣደሰ በመሆኑ፤

WHEREAS, entering into practical application thereof late due to the late ratification and arrival of the amendment proclamation to the region, and because of the fact that all business men of the region and executive bodies haven't obtained full understanding of it, a great many business men haven't yet renewed their license pursuant to the new proclamation;

በዚሁ መሰረት የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘበና አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮችን አስወግዶ ለንግዱ ህብረተሰብ ቀልጣፋ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ምቹና ህጋዊ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has been essential to create favorable and legal condition enabling the business community to provide efficient commercial registration and licensing service by taking in to account the objective reality of the region and avoiding the performance problems encountered to implement the proclamation;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 47 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Regional Government in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58, sub art. 7 of the revised regional constitution, and art 47 of commercial registration and licensing proclamation No. 67/1996, as amended, hereby issues this regulation as follows:

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 21/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 1. Short Title

This regulation may be cited as, "The commercial registration and business licensing proclamation amendment proclamation implementing regulation No.21/2004."

www.abyssinialaw.com



## 2. የእፎይታ ጊዜ እንዲሰጥ ስለመወሰኑ

1. የፌዴራሉ መንግስት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 ዓ.ም. እንደገና /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ /3/ ድንጋጌን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉና ብዛት ያላቸው ነጋዴዎች ደግሞ በተለይ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ዘርፍ የተሠማሩ ሆነው ከመገኘታቸው የተነሣ አዲስ የተተካው ንዑስ አንቀጽ ከሚጥልባቸው ግዴታ ነፃ ለመሆን የሚችሉበት የ15 ቀን የእፎይታ ጊዜ እንዲሰጣቸው በዚህ ደንብ ተወስኗል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የተወሰነው የእፎይታ ጊዜ ከሰኔ 1 ቀን እስከ ሰኔ 15 ቀን 1996 ዓ.ም. ብቻ የሚፀና ይሆናል::

3. ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ፈቃዳቸውን ለማሣደስ የሚቀርቡ ግለሰብ ነጋዴዎችና ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 67/1989 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ /3/ የቀድሞው ድንጋጌ መሠረት ከጥር 1 ቀን እስከ መጋቢት 30 ቀን 1996 ዓ.ም. ያለውን አጠቃላይ ስልሣ በመቶ ውዝፍ ቅጣት በአንድ ጊዜ ከፍለው ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ ይደረጋል::

4. በዚህ የእፎይታ ጊዜ ተጠቅመው ፈቃዳቸውን ያላሣደሱ ግለሰብ ነጋዴዎችና ድርጅቶች በአዋጁ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ /3/ የተሻሻለ ድንጋጌ ስር የተመለከተውን ቅጣት በመክፈል

## 2. Decision to Render Rehabilitation Period

1. Because the re-amended federal government commercial registration and licensing proclamation No.67/1997 is unable to make the provision of art. 25, sub art. 3 practical, and due to the fact that many business men are found being engaged in micro and small scale enterprise commercial streams, it has been decided to provide them with a fifteen days rehabilitation period which enables them to be exempted from the obligation that the newly incorporated sub article may impose on.

2. The rehabilitation period decided pursuant to sub art (1) of this article hereof shall apply only from June 8 to June 22, 2004.

3. Individual business men and organizations who appear to have their license renewed within the rehabilitation period specified hereinabove shall be made to renew same upon the payment of total 60% accumulated penalty for the period starting from December 10, to February 8, 2004, pursuant to the previous provision of art (25), sub art (3) of proclamation No.67/1997, as amended.

4. Individual business men and organizations who haven't renewed their license using such a rehabilitation period shall be duty bound to renew same up to July 7, 2004 upon the payment of the

www.abyssinialaw.com



እስከ ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም. ድረስ የማሳደስ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

5. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በእንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 376/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 7 አማካኝነት አዲስ በተተካው የአዋጁ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ /3/ ድንጋጌ መሠረት የተቀጡና ፈቃዳቸውን በጊዜው ያሳደሱ ግለሰብ ነጋዴዎችና ድርጅቶች ቢኖሩ በዚህ አንቀጽ በተመለከተው የእፎይታ ጊዜ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጎ የከፈሉት የመቀጫ ገንዘብ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ጊዜ ገደብ

ይህ ደንብ የተሻሻለውን አዋጅ መሠረት በማድረግ በወቅቱ ቀርበው የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን ባላሳደሱ ግለሰብ ነጋዴዎችና ድርጅቶች አኳያ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሰኔ 1 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ርዕሰ መስተዳድር

penalty stated under art (25), sub art (3) of the proclamation, as amended.

5. Where there are individual business men and organizations who have been fined and renewed their license pursuant to the provision of article (25), sub article (3) of the proclamation, which is newly incorporated through article (2), sub article (7) of re-amendment proclamation No. 376/2004 before the issuance of this regulation, they shall be made to be beneficiary of the indicated rehabilitation period and the money they have been fined shall be returned to them.

## 3. Time Limit of Application

This regulation shall, on the basis of the amended proclamation, apply only for once on those individual business men and organizations who failed to come and have their working license renewed thereof.

## 4. Effective Date

This regulation shall come in to force starting form June 8, 2004.

Done at Bahir Dar

This 4th day of June, 2004

YOSEF RETTA

Head of Government of the Amhara

National Regional State